# የትብከመ በኩፖን ሥርዓት የግብርና ግብዓት ሽያጭ *የአፈጻጸም መመሪያ (ረቂቅ)*

ጥር 2007 ዓ.ም

መቀለ

## ማውጫ


መግቢያ ..... 3

ክፍል 1 ..... 4

1. የመመሪያው ስያሜ ፤ ..... 4

2. የመመሪያው ዓላማ ..... 4

3. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን ፤ ..... 4

4. የቃላት ትርጓሜ ፤ ..... 4

ክፍል 2 ..... 5

5. የግብርና ግብዓት ሽያጭ ትግበራ ማስፈጸሚያ የአሠራር ሥርዓቶች ..... 5

5.1 የኩፖን ሥርዓት ትግበራውን የሚከታተልና ድጋፍ የሚያደርግ  የቴክኒክ ኮሚቴ ስለማቋቋም ፤ ..... 5

5.2 የግብዓት መረጃና ዋጋ ስለማሳወቅ ፤ ..... 5

5.3 ኩፖን ስለመስጠት፣ ስለመቀበልና ግብዓት ስለማሰራጨት ..... 6

5.4 የኩፖን  ርክክብ ሥርዓት፤ሂሳብ አያያዝ፤ሠነድ ርክክብና ማወራረድ ..... 7

5.5 የማርጅን ክፍያ ፤ ..... 8

5.6 የግብዓት ዝውውርና ክፍያ አፈፃፀም ..... 9

6. ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ቅንጅታዊ ሥራ፣ የመረጃና የሪፖርት ቅብብሎሽ ..... 10

7. በግብዓት አቅርቦት፣ ሥርጭት፣ በብድር አጠቃቀምና አመላለስ ዙሪያ የሚሣተፉ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ..... 11

7.1 በክልል ደረጃ፤ ..... 11

7.2 በዞን ደረጃ ..... 13

7.3 በወረዳ ደረጃ ..... 15

7.4 ቀበሌ  ደረጃ ..... 18

ክፍል አራት ..... 19

8. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ ..... 19

## መግቢያ

የክልሉ መንግስት ለአርሶ አደሩ የሚያስፈልጉ የግብርና ግብዓቶችን መግዣ የሚሆን ብድር በጀቱን ለባንክ በዋስትና በማስያዝ በኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት ሲያቀርብ የቆየ ሲሆን ብድሩ ለአርሶ አደሩ ያስገኘው የልማት ውጤት አበረታች ቢሆንም ከሚሠጠው ብድር ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይመለስ የሚቀረው ገንዘብ ከዓመት አመት እያደገ በመሄዱ ፤ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት መንግስት ለልማት የሚያውለውን በጀት ላልተመለሠ ብድር እየተካ በመሆኑና ይህም በክልሉ በሚከናወኑ የልማት ተግባራት ላይ እያደረሠ ያለው ተጽዕኖ ከፍተኛ እየሆነ በመምጣቱ፣

ይህንኑ ችግር ዘለቄታዊ አሠራር በማመቻቸት እልባት ለመስጠት በተካሄዱ ጥናቶች የግብርና ግብዓት ሽያጩን ለፋይናንስ ተቋማት ማስተላለፍ አስፈላጊ መሆኑ በመረጋገጡ፣

በዚሁ መሠረት ባለፈው የ2006/07 ምርት ዘመን ወደ ተግባር ለማስገባት የሚያስችል በኩፖን ሥርዓት የግብርና ግብዓት ሽያጭ የሙከራ ትግበራ ለማካሄድ በሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ደረጃ የመግባቢያ ሠነድ በመፈራረም አማራ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ጐጀም ዞኖች ሥር በሚገኙ አምስት ወረዳዎች ሁለት ዩኒየኖችና ሃምሳ አምስት ሁለገብ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ደረጃ የተሞከረ ከመሆኑም በላይ በተካሄደው የመርሃ ግብሩ አጋማሽ የአፈፃፀም ግምገማ መሠረት በሂደቱ የተገኘው ውጤት አበረታች ሆኖ በመገኘቱ፣

በሙከራ ትግበራው ወቅት የተገኘውን አበረታች ውጤት መሠረት በማድረግ በሙከራ ትግበራው ሂደት የታዩ ክፍተቶችን በማስተካከል ጥንካሬዎችንና የተሻሻሉ አሠራሮችን በመቀመር ከ2007/08 ምርት ዘመን ጀምሮ በትግራይ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሶስትወረዳዎች ማለትም (አድዋ፣እንዳመሆኒ እና ላእላይ አዲአቦ) የሙከ ራ ትግበራ ለማድረግ ስምምነት ላይተደርሷል:

የክልሉን መንግስት ውሳኔና ያስቀመጠውን አቅጣጫ ለመተግበር ይቻል ዘንድ በአማራ ክልል ወረዳዎች በሙከራ ትግበራው ወቅት የተገኙ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን መሠረት ያደረገ በኩፖን ስርዓት የግብርና ግብዓት ሽያጭ ትግበራ አፈፃፀም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ የትግበራ አፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህም መመሪያ ከሶስቱ ወረዳዎች የሙከራ ትግበራ በሚገኘው ውጠት መሰረት የሚሻሻል ይሆናል።

**ክፍል 1**

## 1. የመመሪያው ስያሜ ፤

ይህ መመሪያ በኩፖን ሥርዓት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብአት ሽያጭ ትግበራ አፈጻጸም መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

## 2. የመመሪያው ዓላማ

በክልሉ መንግስት ውሳኔ መሰረት የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት እንዲያስተዳድሩት የተደረገው በኩፖን ስርአት የግብአት ሽያጭ አርሶ አደሩን ተደራሽና ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ በሚመለከታችው አስፈጻሚ አካላት የተናጠልና የጋራ ርብርብ በተቀላጠፈና በተዋጣለት መንገድ እንዲፈጸም በማድረግ የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ገቢ ማሳደግ ነው፡፡ በተጨማሪም የብድር አመላለሱን በማሻሻል የመንግስት ገንዘብ ለዕዳ መተኪያ እንዳይውል ማድረግ ነው፡፡

## 3. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን ፤

ይህ የአፈጻጸም መመሪያ በኩፖን ሥርዓት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብአት ሽያጭ ትግበራ እንዲካሄድ በተወሰነባቸውና ወደፊትም በሚወሰንባቸው ዞኖችና ወረዳዎች እንዲሁም በግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት በሚሳተፉ ሁለገብ ኅብረት ሥራ ዩኒየኖችና ሁለገብ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት እና ቅርንጫፎቻቸው ደረጃ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. የቃላት ትርጓሜ ፤

**የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓት ማለት፤** ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያገለግሉ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ የምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጅዎችና ቁሳቁሶች ማለት ነው

**ኩፖን ማለት፣** የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት እጅ በእጅም ሆነ በብድር ግብዓቱን ለሚገዙ አርሶ አደሮች ግብዓቱን ከሚያቀርቡ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት እንዲረከቡ የሚሰጠው የግብዓቱ ዓይነት፣ መጠን፣ ዋጋው እና የተቀባዩ ስም የተጻፈበት ሠነድ ነው፡፡

**ማርጅን ማለት፣** መሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት፣ ዩኒየኖች እና የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት በግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ሂደት ውስጥ የሚያወጡትን ወጪ ለማካካስ የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡

የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት **ማለት፣** የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎቶች ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲያደርሱ ቀበሌዎችን ባማከለ ደረጃ የተቋቋሙ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡

**የግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ማለት፣** የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ ስርጭትና ብድር አመላለስ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ተግባሩን በበላይነት ለመምራት የሚመለከታቸውን አካላት በአባልነት ያቀፈ በየደረጃው የተቋቋመ አካል ነው፡፡

**ቴክኒክ ኮሚቴ ማለት፣** በየደረጃው ከሚገኙ አካላት ከግብርና፣ ከህብረት ስራ ማህበራት፣ ከየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት የተውጣጡ ባለሙያዎችን ያቀፈ ሆኖ የግብዓት አቅርቦት፣ ስርጭትና ብድር አመላለስ ተግባር ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ኮሚቴ ነው፡፡

**የሁለገብ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር ቅርንጫፍ ማለት፣** በግብርና ግብዓት ሽያጭና በግብርና ምርት ግዥና ሽያጭ አርሶ አደሩን ተደራሽ ለማድረግ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት የከፈቷቸው ተጨማሪ የአገልግሎት መስጫ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡

## ክፍል 2

## 5. የግብርና ግብዓት ሽያጭ ትግበራ ማስፈጸሚያ የአሠራር ሥርዓቶች

### *5.1 የኩፖን ሥርዓት ትግበራውን የሚከታተልና ድጋፍ የሚያደርግ የቴክኒክ ኮሚቴ ስለማቋቋም ፤*

1. ባለፉት ዓመታት የወጣው የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት እንዲሁም ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭትና አመላለስ ትስስር አስተዳደር መመሪያ ላይ በተመለከተው መሠረት በየደረጃው የተቋቋመው የግብርና ግብዓትና ብድር አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የኩፖን ሥርዓቱን የሚከታተልና የሚደግፍ የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ በየደረጃው የኩፖን ሥርዓት ትግበራውን የሚከታተልና የሚደግፍ የቴክኒክ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡
2. በየደረጃው የሚቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ የሚከተሉትን በአባልነት ያካትታል/ያቅፋል፡፡ ተጠሪነቱም በየደረጃው ለተቋቋመው የግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡
   - 2.1. በየደረጃው የሚገኙ የግብርና አካላት ግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት እንዲሁም ብድር አመላለስ የስራ ሂደት አስተባባሪ
   - 2.2. በየደረጃው የሚገኙ የኅ/ሥ/ማ/ማስ/ የስራ ሂደት አስተባባሪ፣
   - 2.3. በየደረጃው የሚገኙ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት የደንበኛ ግንኙነት የስራሂደት አስተባባሪ፣
   - 2.4. በየደረጃው የሚገኙ የገ/ኢ/ል/ቢሮ፣በክልል ደረጃ ትሬዠሪ አስተዳደርና ሂሳብ ማጠቃለያ የስራ ሂደት አስተባባሪ/በዞንና በወረዳ የክፍያና ሂሳብ ማጠቃለያ የስራ ሂደት አስተባባሪ/
3. የቴክኒክ ኮሚቴውን በኃላፊነት በየደረጃው የግብርና አካላት በሰብሳቢነት እንዲመሩት ይደረጋል፡፡ ኮሚቴው ፀኃፊ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ተወካይ ይሆናል
4. በየደረጃው የሚቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡
   - 4.1. በኩፖን ሥርዓት ለአርሶ-አደሩ እጅ በእጅና በብድር የሚሠራጨውን ግብዓት ለመከታተል ለመደገፍ የሚያስችል ዕቅድ ያዘጋጃል፣
   - 4.2. በሚዘጋጀው ዕቅድና ቸክ ሊስት መሰረት ትግበራውን ይከታተላል፤ ይደግፋል፣
   - 4.3. ትግበራውን አስመልክቶ በአፈፃፀም ወቅት ለሚነሱ ጥያቄዎች መመሪያን መሠረት በማድረግ ማብራሪያ ይሰጣል፣
   - 4.4. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የግንዛቤ መድረኮችን በማዘጋጀት በፈፃሚ አካላት ዘንድ ግንዛቤ ይፈጥራል
   - 4.5. የትግበራውን አፈፃፀም ከቅድመ-ዝግጅት ጀምሮ በትግበራ ሂደት የታዩ ጥንካሬዎችንና ክፍተቶችን አስመልክቶ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፤ ለተጠቃሚዎች ያስተላለፋል፣
   - 4.6. የኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ በየሳምንቱ በሚደረግ ስብሰባ ይገመግማል፤ በየአስራ አምስት ቀኑ በኮሚቴው ሰብሳቢ አማኝነት በየደረጃው ለሚገኘው የግብአት አስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

### *5.2 የግብዓት መረጃና ዋጋ ስለማሳወቅ ፤*

1. በአሰራርና በመርህ ደረጃ በዩኒየኖችም ሆነ በመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት መጋዘን ግብዓት ተርፎ መክረም የለበትም

2. ከላይ የተገለጸው ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቶ ግብአት ተርፎ ካደረ ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የግብዓት ሥርጭት ከመጀመሩ በፊት በመጋዘናቸው የሚገኘውን የከረመና በዘመኑ የቀረበ ግብዓት በአግባቡ ቆጠራ በማከናወንናበመከዘን በገባበት ምርት ዘመን፣ በዓይነት፣ በመጠንና በብር በወቅቱ ከሚኖረው ዋጋ ጋር መረጃውን አጥርተው በመያዝ ለወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶችና ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተ/ጽ/ቤቶች በህጋዊ ደብዳቤ ያሳውቃሉ፡፡

3. ከላይ በተገለፀው መሠረት የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶችና ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጽ/ቤትም የግብዓት መረጃውን በጋራ በመስራትና በማጠቃለል ለወረዳው የግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴና ለዞን ግብርናና ህብረት ስራ ተጠሪ ጽ/ቤት ይልካሉ፡፡ ፤ የዞን ግብርናና ህብረት ስራ ተጠሪ ጽ/ቤቶችም መረጃውን በጋራ በማጠናቀር ለዞን ግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴና ለክልሉ ግብርና ቢሮና ኅብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ ያሳውቃሉ፡፡

4. ለክልሉ ግብርና ቢሮም የደረሰውን የከረመና በምርት ዘመኑ የቀረበ ግብዓት መረጃ ከክልሉ ኅብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ ጋር በጋራ በማጠቃለል በግብርና ቢሮ አማካኝነት ለክልሉ ግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያሳውቃል፡፡

5. የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮም መረጃውን የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ዋናው መ/ቤት በማሳወቅ የገንዘብ አመላለስ ሥርዓቱ በአግባቡ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

6. የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ዋና መ/ቤትም በደረሰው መረጃ መሰረት ግብዓቱን እየሸጠ ገቢ እንዲያደርግበት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በተገለጸለት የባንክ ሂሳብ ቁጥር መሰረት በየምርት ዘመኑ ገንዘቡን ገቢ ያደርጋል፡፡

7. ግብዓትን በተመለከተ በየደረጃው የሚገኙና የሚመለከታቸው አካላት የጋራ ያደረጉትን መረጃ በመደበኛው አሰራር መሰረት ተጠሪ ለሆኑበት ተቋም ያስተላልፋሉ ፤

8. ሁለገብ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የግብአት ዋጋ ለውጥ በሚኖርበት ወቅት የዋጋ ለውጡን በግብአት አይነት በመዘርዘር ለየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት በህጋዊ ደብዳቤ በየጊዜው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

9. የየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራትም ከሁለገብ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በሚደርሳቸው የዋጋ ለውጥ መረጃ መሠረት በኩፖን ሥርዓት አርሶ አደሩን ያስተናግዳሉ፡፡

10. ይህ መመሪያ ተፈጻሚ እንዲሆን በተደረገባቸው ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ በኩፖን ስርአትና የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ተሳታፊነት ብቻ እንዲከናወን ይደረጋል፤በቀድሞው አሰራር ግብአት ማሰራጨት አይቻልም፡፡

## *5.3 ኩፖን ስለመስጠት፣ ስለመቀበልና ግብዓት ስለማሰራጨት*

1. አርሶ አደሩ የሚፈልገውን የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብአት ፍላጎት ጥያቄ ለየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ያቀርባል፡፡

2.የአርሶ አደሩ የግብአት ጥያቄ በእጅ በጅ ግዥ ከሆነ ለግብአቱ መግዥያ የሚሆነውን ገንዘብ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ሰራተኞች በመክፈል የእጅ በጅ ሽያጭ ኩፖን ይረከባል

3.የአርሶ አደሩ የግብአት ጥያቄ በብድር ግዥ ከሆነ አስፈላጊውን የብድር መመልመያ መስፈርት በማሟላት ለግብአቱ መግዥያ የሚሆነውን ቅድሚያ ክፍያ ለየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ሰራተኞች በመክፈል የብድር ሽያጭ ኩፖን ይረከባል

4. እጅ በጅም ሆነ በብድር ለሚቀርብ የግብአት ጥያቄ ኩፖን በጥንቃቄ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን አርሶ አደሩ በተናጠልም ሆነ በጋራ እስከ ሰባት ሰው ድረስ በመሆን  በአንድ ኩፖን (የመጀመሪያውን ቅጅ በመጠቀም) ግብአት ይሰጠዋል

5. አረሶ አደሩ በተቀበለው ኩፖን ልክ ግብአቱን  ወዲያውኑ ከመሠረታዊ  ህብረት ስራ ማህበራት ሽያጭ ሠራተኛ ቀርቦ የመረከብ ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚፈጠረው ክፍተት አርሶ አደሩ ተጠያቂ ይሆናል

6. የሁለገብ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትና ቅርንጫፎቻቸው አርሶ-አደሩ የሚሰጣቸውን ኩፖን ሰለትክክለኛነቱ በማረጋገጥ እየተቀበሉ በኩፖን ውስጥ በተዘረዘረው የግብዓት ዓይነትና መጠን መሠረት ለአርሶ-አደሩ ግብዓቱን ያስረክባሉ፣

7. ለአርሶ-አደሩ የሚሠራጨውን ግብዓት ገቢና ወጪ በተመለከተ አሠራሩ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በሚመሩበት የንብረት ገቢና ወጪ ሥርዓት መሠረት ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፣

8. የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሽያጭ ሠራተኞች ከአርሶ-አደሩ የሰበሰቡትን ኩፖንና ያሰራጩትን ግብዓት መጠን በየዕለቱ በማመዛዘን ያረጋግጣሉ፣

9. ከላይ በተገለፀው መሠረት ሽያጭ ሠራተኞች ከአርሶ አደሩ ያሰባሰቡትን ኩፖን በአግባቡ በመያዝ እንደ ኩፖኑ መብዛትና ማነስ በየቀኑ ወይም በየሁለት ቀኑ ለማኅበሩ ሂሳብ ሠራተኛ አስመዝግቦ ለገ/ያዥ ገቢ ማድረግና ማረጋገጫ መቀበል ይኖርባቸዋል፣

### *5.4 የኩፖን ርክክብ ሥርዓት፣ሂሳብ አያያዝ፣ሠነድ ርክክብና ማወራረድ*

1. በሚያመች መንገድ ካጠናከሩ በኋላ በማህበሩ ግንዘብ ያዥ አማካይነት በሸኝ ደብዳቤ ኩፖኑን ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት  ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያስረክባሉ
2. በመሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራትና በገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት  መካከል የኩፖን ርክክብ ቢያንስ በ15 ቀናት ውስጥ አንድ ጊዜ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት በወቅቱ ኩፖን ሳያስረክቡ ቀርተው ለሚፈጠረው ክፍትት ተጠያቂ ይሆናሉ
3. የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት ለተረከበው ኩፖን የእጅ በእጅና በብድር በመለየት  ህጋዊ ደረሰኝ መስጠት ይጠበቅበታል
4. የኩፖን ርክክቡ ሲፈፀም በኩፖኑ ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን የዩኒዬንና መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን የማርጅን ከፍያን እንደሚያካትት መታወቅ አለበት
5. የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ገንዘብ ያዥ ከገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት  ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተሰጠውን ደረሰኝ ለመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበሩ በማቅረብ ሂሳቡን ያወራርዳል፡ ከእዳ ነፃ ይሆናል
6. ሁለገብ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽቤት የተረከቡትን ደረሰኝ በቂ ኮፒ በማድረግና ከዋናው ጋር የተገናዘበ መሆኑን በማረጋገጥ ከዝርዝር የሂሳብ ሪፖረት ጋር በመሸኛ ደብዳቤ የዱቤ ሽያጭ ለፈጸመላቸው ዩኒየን፣ለወረዳ ግብርና ጽ/ቤትና ለወረዳ ህብረት ስራ ማህበራት ተጠሪ ጽቤት ሪፖረት ያቀርባሉ፡፡
7. ዩኒዬኑ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በተረከበው ደረሰኝና ዝርዝር ሪፖርት መሠረት የግብዓት ሽያጩን ያከናወነው ሳተላይት ጽ/ቤት ተጠሪ በሆነው የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ፕሮግራም በማስያዝና በመሄድ

በየመሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበሩ ስም ሂሳባቸውን ያመሳክራል፤ የመሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትን የዱቤ ሽያጭ እዳ የሂሳብ ማስተካከያ በመስራት እዳ ያቀናንሳል፤ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤትም በዩኒየኑ ስም ወደ ባንክ ተመላሽ ያደረገበትን የባንክ ደረሰኝና ተያያዥነት ያለቸውን ሰነዶች ለዩኒየኑ ያቀርባል፡፡

8. በገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ደረጃ ከተሰበሰበው የግብዓት ገንዘብ ውስጥ መንግስት ቀድሞ ለባንክ የከፈለውና ከወረዳ በጀት የተቀነሰ መሆኑን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሚያሳውቀው መሠረት ለወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ገቢ ያደርጋሉ

9. መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት እና ዩኒዬኖች መረጃቸውን በማደራጀት በኅብረት ሥራ ማኅበራት ሂሳብ አያያዝ መመሪያ መሠረት ለኦዲት ዝግጁ ይሆናሉ፣

10. የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት ከተለያዩ ቅርንጫፎች እጅ በእጅ ሽያጭና በቅድሚያ ክፍያ የተሰበሰበውን የግብዓት ገንዘብ በወቅቱ በዩኒየኑ ስም በየምርት ዘመኑ ለይቶ ለባንክ ተመላሽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

11. የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለየምርት ዘመኑ የግብዓት ብድር ተመላሽ የሚደረግበትን የባንክ ሂሳብ ቁጥር የግብዓት ስርጭት ከመጀመሩ በፊት ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ማሳወቅ አለበት፡፡

12. የግብዓት ዝውውር ተፈጽሞ ክፍያ እንዲፈጸም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መረጃው እንደደረሰው ጊዜው ከማለፉ በፊት የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ክፍያ እንዲፈጽም ያደርጋል፡፡

13. የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዩኒዬኖች ስም ወደ ባንክ ተመላሽ የሚያደርጉት ገንዘብ የምርት ዘመኑንና የገንዘብ መጠኑን በግልፅ መፃፍ ይኖርበታል፡፡

14. ለግብዓት ስርጭቱ የሚታተመው ኩፖን በአራት ቅጅ ሆኖ የግብዓቱን ዓይነት፣ መጠን እና ጠቅላላ ዋጋ በሚያሳይ መልኩ መታተም አለበት፡፡

15. የኩፖን ስርጭቱ

- የመጀመሪያውን ቅጅ አርሶ አደሩ ለግብዓት መረከቢያ ለማህበሩ ሽያጭ ክፍል፣
- ሁለተኛው ቅጅ ለመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበሩ ሂሳብ ሠራተኛ፣
- ሦስተኛው ቅጅ ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ሂሳብ ክፍል፣
- አራተኛው ቅጅ ከፓዱ ጋር ቀሪ ይሆናል፡፡

*5.5* የማርጅን ክፍያ ፤

1. ለዩኒየኖችም ሆነ ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በወቅቱ የተፈቀደላቸው ማርጅን መጠን የክልሉ ግብርና ቢሮ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በደብዳቤ ያሳውቃል፤
2. የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮም በየደረጃው ላሉ ማህበራትና ዩኒየኖች ከግብርና ቢሮ በሚደርሰው መረጃ መሰረት ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ዋና መ/ቤት የማርጅን ክፍያ እንዲፈጽም ያሳውቃል፡፡
3. በመሠረታዊ ማህበራትና በገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤቶች ደረጃ የኩፖን ርክክቡ እንደተጠናቀቀ የማርጅን ክፍያ በገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት አማካኝነት ይፈፀማል፡፡

4. የዩኒየኖችም ሆነ ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚከፈለው ማርጅን ብር በአንድ ኩንታል ሂሳብ ተሰልቶ ይሆናል ፤

5. ለዩኒየኖችም ሆነ ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በሚመለከተው አካል ከተፈቀደላቸው ማርጅን በላይ መጠየቅ አይችሉም፤

6. የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት ለዩኒየኖችም ሆነ ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚከፈለው ማርጅን ለዩኒየን ወይም ለመሠረታዊ ማኅበራት የተፈጸመ ክፍያ በሚል በስም ተለይቶ በሚቀርበው አግባብ ይሆናል

## *5.6 የግብዓት ዝውውርና ክፍያ አፈፃፀም*

1. በየምርት ዘመኑ የሚቀርበው የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓት በመርህ ደረጃ የአርሶ አደሩን ፍላጎት መሠረት ባደረገና በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ መፈፀም ስላለበት የግብዓት ዝውውር መፈፀም የሚደገፍ አይደለም፣

2. ከላይ የተገለፀው አሠራር ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቶ የግብአት ዝውውር መፈጸም ግዴታ ሆኖ ከተገኘ በቅድሚያ ዝውውሩን በየደረጃው የሚገኙ የግብዓትና ብድር አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲያውቀውና እንዲወስን መደረግ አለበት፣

3. ዝውውሩ እንዲፈፀም ከተፈቀደ ግብዓቱ በዓይነትና በመጠን ተለይቶ እንዲሁም በብር ተሰልቶ በተቀባይና ሰጪ አካላት አማካኝነት በሚፈፀም ስምምነት መሠረት ይፈፀማል፣

4. የግብዓት ዝውውሩ በአንድ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ደረጃ የሚፈፀም ከሆነ ጥያቄውን ያቀረበው መሠረታዊ ማኅበር የማጓጓዣ ወጪውን ከፍሎ ግብዓቱን ያጓጉዛል፣ ዩኒየኑም ዕዳ ምዝገባውን ማስተካከል ይኖርበታል

5. ግብዓቱን የወሰደው መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር የማጓጓዣ ወጪውን ከግብዓቱ ዋጋ ላይ ደምሮ ለየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት እንዲያሳውቅ በማድረግ ግብዓት ለተጠቃሚዎች እጅ በእጅም ሆነ በብድር ሲሸጥ የማጓጓዣ ወጪው መጨመሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፣

6. መሠረታዊ ማኅበሩ ለማጓጓዣ ያወጣውን ወጪ ማስረጃ ኮፒ በማድረግ አረጋግጠው ለወረዳው ግብርና ጽ/ቤት፣ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት፣ ለህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ተ/ጽ/ቤት እና ለዩኒዬ ያሳውቃሉ፣

7. የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በሚደርሰው መረጃ መሠረት ዝውውሩ በተፈጸመበት የሥራ ክልል የሚገኘው የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የማጓጓዣ ወጭውን እንዲከፍለው በህጋዊ ደብዳቤ ያሳውቃል ፤ መረጃው የደረሰው የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤትም ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ክፍያውን ይፈጽማል ፡

8. ለተፈጸመው ዝውውር ለአቅራቢ ዩኒዬኑ በሚደርሰው ህጋዊ ማስረጃ መሠረት ዕዳ አመዘጋገቡን በዝውውሩ አፈፃፀም መሠረት ያስተካክላል፣

9. ከዩኒየኑ የስራ ክልል ውጭ የሚፈፀም የግብአት ዝውውር ሰምምነት የኩፖን ስርአቱን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ በዱቤ ሽያጭ ብቻ ይሆናል፡፡

10. ከዩኒየኑ የስራ ክልል ውጭ የሚፈፀም የግብአት ዝውውር ስምምነት ከተደረሰ በኋላ ጠያቂው ዩኒዬን የማጓጓዣ ወጪውን በመክፈል ግብዓቱ ወደተፈለገበት መሠረታዊ ማኅበር ያጓጉዛል፡፡ የግብዓቱን ዋጋ፣ ማርጅንና የማጓጓዣ

ወጪውን በማካተትና ለይቶ በማሳየት ዝርዝሩን ለመሠረታዊ ማኅበሩ በተለመደው አግባብ በዕዳነት በመመዝገብ ያስረከባል፡፤ ይህንኑ መረጃ በሽያጩ ለሚሳተፈው የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ቅ/ጽ/ቤት ያሳውቃል

11. ከዩኒየኑ የስራ ክልል ውጭ በዱቤ ሽያጭ በዝውወር የቀረበ ግብአት ወዲያውኑ ለሽያጭ አገልግሎት መዋል ይኖርበታል

12. በዱቤ ሽያጭ በዝውውር የቀረበው ግብአት በቀረበለት መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበር የስራ ክልል የሚገኘው የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት በአቅራቢው ዩኒየን በሚቀርበለት ህጋዊ ማስረጃ መሰረት የማጓጓዣ ወጪውንና ማርጅኑን ይከፍላል

13. የግብአቱን የሽያጭ ዋጋ የዱቤ ሽያጭ በፈጸመው ዩኒየን ስም ዩኒየኑ በሚገኝበት አካባቢ የሚገኝ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ቅ/ጽ/ቤት በሻጭ ኒየን ስም ባንክ እንዲያስገባ እንዲሁም የመጋዝን ኪራይ እና ሌሎች ወዎጭች ካሉበት በቀረበው ዝርዝር መሠረት እንዲከፈል በሃዋላ ያስተላልፋል፤ የሃዋላ ወጭውን ከግብአት አቅራቢው ዩኒየን ከማርጅን ክፍያው ላይ ይቀንሳል፡፡

14. የዱቤ ግዥ የፈፀመው ዩኒየን ገንዘቡን ለሻጭ ዩኒየን ካስተላለፈለት የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ቅ/ጽቤት ማዘዣ ሰነድ በመያዝ የተላለፈው ገንዘብ በሻጭ ዩኒየን ስም ባንክ መግባቱን በመከታተል መረጃው ከሻጭ ዩኒየን እንዲደርሰው ያደርጋል፤ በሚደርሰው መረጃ መሰረትም የዱቤ ግዥ እዳውን ከውል ስምምነቱ ጋር በማያያዥ እዳውን ያቀናንሳል፡፡

ከዩኒየን ዩኒየን ውጭ ዩኒየኖች ከመሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ግብአት በዱቤ ማዘወር ካስፈለጋቸው ከላይ በተራ ቁጥር 13 እና 14 በተገለጸው አግባብ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ክፍል 3**

## 6. ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ቅንጅታዊ ሥራ፣ የመረጃና የሪፖርት ቅብብሎሽ

1. የግብርና ግብዓት ሽያጭ የኩፖን ሥርዓት ትግበራውን በማስፈፀም በኩል የአስተዳደር፣ የግብርና፣ የኅብረት ሥራ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት፣ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት አካላት በየደረጃው ባላቸው አደረጃጀት መሠረት ለትግበራው መሳካት የበኩላቸውን ድጋፍ ያደርጋሉ፣

2. በየደረጃው በሚቋቋሙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ውስጥ በየተቋማቱ በሚወከሉ አባላት አማካኝነት በኩፖን ሥርዓት የግብዓት ሽያጭ ትግበራው በቅንጅትና በትብብር ይደገፋል ፣

3. የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤቶች በግብዓት ሥርጭት ትግበራው በሚሳተፉ በእያንዳንዱ መሰረታዊ ማህበር እና ቅርንጫፎቻቸው እንዲቋቋሙ ይደረጋል፣

4. በትግበራው ሂደት የሚሳተፉ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትና ቅርንጫፎቻቸው እንዲሁም የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤቶች ግብዓቱን በማሰራጨት ሒደት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የሆነ አደረጃጀት ይኖራቸዋል፣

5. በየደረጃው የሚገኙ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤቶች የግብዓት ስርጭቱን በሚመለከት ከመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ጋር በየቀኑ መናበብ ይኖርባቸዋል፡፡

6. ከወረዳ ጀምሮ በዞንና በክልል ደረጃ የሚቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ የኩፖን ሥርዓቱን አፈጻጸም በሚመለከት በየሳምንቱ እየተገናኙ ይገመግማሉ፣ ለሚመለከተው አካልም ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## 7. በግብዓት አቅርቦት፣ ሥርጭት፣ በብድር አጠቃቀምና አመላለስ ዙሪያ የሚሣተፉ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 7.1 *በክልል ደረጃ፤*

**የክልል አስተዳደር ም/ቤት፤**

- ✓ በግብርና ቢሮ፤ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተጣርቶ የሚቀርበውን የግብዓት ብድር ፍላጎት የውሣኔ ሃሣብ መርምሮ ያጸድቃል፤
- ✓ የክልሉን በጀት ዋስትና በማስያዝ ብድር እንዲፈቀድ ያደርጋል፤
- ✓ የግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴውን ይመራል፣ ያስተባብራል።
- ✓ ከገ/ኢ/ል/ቢሮ በሚቀርብለት መረጃ መሰረት ለባንክ ያልተመለሰ ብድር ሙሉ በሙሉ እንዲመለስ ያደርጋል።
- ✓ ከክልሉ ግብርና ቢሮ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የማኅበራትን ማርጅን ይወስናል የክልሉ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ዋናው መስሪያቤት በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት በኩፖን ስርአት የግብአት ሽያጭ ሲፈፅም የሚያወጣቸውን ወጭ የሚሸፍን በቂ በጀት ይወስናል፡፡

**የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ (ATA)**

- ✓ ዘላቂ የግብርና ግብዓት ስርጭት፣ ተደራሽነትንና መጠን ለማሳደግ እንዲሁም የገጠር ፋይናንስ አገልግሎት ለማሳደግ የሚያስችል ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ተስማሚ ስርዓት ይቀረጻል፣ ለአፈጻጸሙ ቴክኒካል፣ የአመራር ና የፋይናንስ ድጋፍ ያፈላልጋል፡

**በየደረጃዉ ያሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መዋቅር**

- ✓ በሚመሰረተዉ የብድር ዋስትና ፈንድ መሰረት ለግብርና ግብዓት ብድር የሚዉል ገንዘብ ያቀርባል፤
- ✓ በሀገር ደረጃ በሚደረግ የግብርና ግብዓት ብድር የጋራ ኮሚቴ ሥራዎች ላይ ተሳትፎ ያደርጋል፤
- ✓ ስለ ግብርና ግብዓት ብድር አስፈላጊውን መረጃ ይይዛል፣ ያሰራጫል፤
- ✓ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ከተለያዩ ቅርንጫፎች እጅ በእጅ ሽያጭና በቅድሚያ ክፍያ የተሰበሰበውን የግብዓት ገንዘብ በዩኒየኑ ስም በየምርት ዘመኑ ለይቶ ለባንክ ተመላሽ ሲያደርግ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣል፤ ሂደቱን ይደግፋል፡፡

**የግብርና ቢሮ ፤**

- ✓ ስራውን በበላይነትና በሃላፊነት መምራት: መከታተልና: መፈጸም
- ✓ በአጠቃላይ ስለ ግብዓት ብድር አሰጣጥና አጠቃቀም በተመለከተ የሚወጡ መመርያዎች በአርሶ አደሩ ግንዛቤ እንዲያድርባቸው ማድረግና የማስተማር ሃላፊነት ይኖረዋል
- ✓ የገጠር ልማት ፖሊሲንና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ አጠቃላይ የግብርና ልማት አቅጣጫን የሚያሳይ ዕቅድና የሚያስፈልጉ የግብርና ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን እንዲሁም የመፈጸም አቅምን በማገናዘብ ክልላዊ ይዘት ያለው ዕቅድ ያዘጋጃል፤
- ✓ የግብርና ግብዓቶች መግዣ የሚውል ብድር በወቅቱ እንዲፈቀድና በስራ ላይ እንዲውል ማድረግ ፤
- ✓ የግብዓት አቅርቦት ፣ ስርጭትና አጠቃቀም ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ የሚያስችል የአሰራር ስልት መንደፍ ፣ መከታተልና ውጤቱን መገምገም

- ✓ የከረመ ግብዓትን በተመለከተ ከዞን በሚደርሰው መረጃ መሰረት ከክልሉ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ጋር በጋራ በማጠናቀር ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያሳውቃል ፤
- ✓ ዝውውር እንዲፈጸም የተጠየቀ ግብዓት ወደሚፈለገው ቦታ ዝውውር እንዲፈጸም ያደርጋል
- ✓ ወደ ግብዓት ግብይቱ የሚገቡ ዩኒየኖችን እና የማርጅን አወሳሰን ከህ/ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ጋር በጋራ ይሰራል ፤
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- ✓ በክልል ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል፣

**ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፤**

- ✓ በግብርና ቢሮ የሚቀርበውን የግብዓት መግዣ ብድር ጥያቄ ለክልል ምክር ቤቱ በወቅቱ በማቅረብ እንዲፀድ በማድረግና ከባንክ ጋር የብድር ስምምነት ይይዛል፡፡
- ✓ በምርት ዘመኑ የተሰጠውንና የተመለሰውን የብድር ገንዘብ መረጃ በተቡዳሪ ዩኒየንና በየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት መካከል ያለውን በማጥራት በወቅቱ ሂሳቡ እንዲጠቃለል ያደርጋል
- ✓ ከግብርና ቢሮ የሚቀርብለትን የግብዓት ዝውውርና የከረመ ግብዓት ክፍያ መሠረት በማድረግ ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት በወቅቱ በማቅረብ ክፍያ እንዲፈጸም ማድረግ
- ✓ በመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትና በየገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት የሚሰጠውን የዕጅ በዕጅና የብድር ሽያጭ መረጃ ከተቋማቱ በማሰባሰብ ከባንክ ጋር መረጃ የማስታረቅ ሥራ ይሰራል
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ በክልል ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል ;

**ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ**

- ✓ የግብዓት ስርጭት ስልት በመንደፍ ከሚመለከታችው ጋር በመሆን ተግባራዊነቱን ይከታተላል
- ✓ ለማህበራቱ የቀረበው ግብዓት በጥንቃቄ መያዙን ይከታተላል
- ✓ ማህበራቱ ጠንካራ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንዲኖራቸው ሙያዊ ድጋፍ ያደረጋል፤ ይቆጣጠራል
- ✓ ስለ ግብዓት ሽያጭ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይይዛል ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል፤
- ✓ ትምህርትና ስልጠና ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል
- ✓ መሰረታዊ ማህበራትና ዩኒየኖች ያለባችውን የመጋዘን እጥረት ለማስወገድ በራሳቸው ይሁን ሌላ በጀት በማፈላለግ ግንባታ እንዲካሄድ ድጋፍ ደርጋል፣
- ✓ ወደ ግብዓት ግብይቱ የሚገቡ ዩኒየኖችን እና የማርጅን አወሳሰን ከግብርና ቢሮ ጋር በጋራ ይሰራል ፤
- ✓ የከረመ ግብዓትን በተመለከተ ከክልሉ ግብርና ቢሮ ጋር በጋራ መረጃ ያጠናቅራል፤ ለታችኛው መዋቅር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ በክልል ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት **ዋና መ/ቤት፤**

- ✓ የግብዓት ሽያጭና ብድር አመላለሱን የሚመለከት እራሱን የቻለ የትግበራ መመሪያ ያዘጋጃል፣
- ✓ ከህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ በሚደርሰው መረጃ መሰረት ሳተላይት ጽ/ቤቶች የሚከፈቱባቸውን ቦታዎች ለይቶ ለአካባቢ ጽ/ቤቶች ያሳውቃል፣
- ✓ ለግብርና ግብዓት ሽያጩ እና ብድር አመላለሱ በሳተላይት ጽ/ቤት ደረጃ ለሚመደቡ ሠራተኞች ስልጠና ይሰጣል
- ✓ ለተግባሩ አስፈላጊ የሆነ ግብዓቶችን ካዝና፣ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች፣ ኩፖን፣ የኩፖን መረከቢያ፣ የገንዘብ መቀበያና መክፈያ ደረሰኞች፣ ቅጻቅጾች በበቂ መጠን ገዝቶ ያቀርባል፣
- ✓ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሚደርሰው መረጃ መሰረት የግብርና ግብዓት ሽያጭ ገንዘብ በዩኒኖች ስም ተመላሽ የሚደረግበትን የባንክ ሂሳብ ቁጥር ለአካባቢ ጽ/ቤቶች ያሳውቃል፡፡
- ✓ ከግብርና ቢሮ በሚደርሰው መረጃ መሰረት የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት፣ የዩኒየኖች እና የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራትን ማርጅን ለአካባቢ ጽ/ቤቶች ያሳውቃል፡፡
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል በክልል ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

### *7.2 በዞን ደረጃ*

#### *የዞን አስተዳደር*

- ✓ የዞኑን ግብዓትና ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀምና አመላለስ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲከናወን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይገመግማል፣ ይወስናል፤
- ✓ የግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴን ያስተባብራል፣ ይመራል
- ✓ ሕገወጥ የግብዓት ንግድና ዝውውርን ይቆጣጠራል፤
- ✓ የዩኒየኖችን ማርጅን በዞኑ ግብአት አስተባባሪ አማካይነት እንዲወሰን ያደርጋል
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

#### *የዞን ግብርና መምሪያ*

- ✓ የግብርና ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን እንዲሁም የመፈጸም አቅምን በማገናዘብ ዞናዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

- ✓ በየወረዳው የተሰጠውን እና የተመለሰውን እንዲሁም ቀሪ ብድር መረጃ በጠራ መልክ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይይዛል፤ የዩኒየኖችን ማርጅን በዞኑ ግብአት አስተባባሪ አማካይነት እንዲወሰን ድጋፍ ይሰጣል
- ✓ የታቀደ ግብዓትና ብድር በአርሶ አደሩ ፍላጎትና የመፈጸም አቅም እየታየ እንዲቀርብና በሥራ ላይ እንዲውል ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤
- ✓ በየወረዳው ያልተሰራጨ ግብዓት በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከወረዳ ወረዳ ያዛውራል፤ እንዲሁም በዞኑ ውስጥ ሊሰራጩ ያልቻሉትን ወደ ሌላ ዞን እንዲዛወር ጥያቄውን ለክልል ግብርና ቢሮ ያቀርባል፤
- ✓ አርሶ አደሩ የወሰደውን ግብዓት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ይከታተላል፤
- ✓ በምርት ዘመኑ ሳይሰራጭ የከረመ ግብዓት በጥንቃቄ እንዲያዝ ያደርጋል መረጃ ያስተላልፋል ፤ የሚወገድ ግብዓት ሲኖርም ጥናት አካሂዶ ለአስተባባሪ ኮሚቴው አቅርቦ ያስወስናል፤
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ በዞን ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

**የዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ**

- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ የዘመኑና ውዝፍ የብድር አመላለስ መረጃ ከአበዳሪ አካላት በሚሰጠው መረጃ መሰረት በጠራ መልኩ ይይዛል፣ የተሰጠውንና የተመለሰውን ብድር በመለየት ለክልሉ ገ/ኢ/ልማት ቢሮ ፣ለዞን አስተዳደር፣ ሪፖርት ያደርጋል።
- ✓ ከተሰጠው ብድር ውስጥ ለባንክ የተመለሰና ቀሪ ብድር መረጃን በበጀት ዓመት፣ በምርት ዘመን፣ በአበዳሪ አካላት ለይቶ ይይዛል ፣ መረጃውንም በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል።
- ✓ በዞን ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

**የዞን ህ/ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ተጠሪ ጽ/ቤት**

- ✓ የግብዓት አቅርቦት፤ ስርጭት አጠቃቀምና አመላለስ ተግባራዊነቱን የዞን ግብርና መምሪያ ጋር ይከታተላል
- ✓ ማህበራቱ ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጉ ድጋፍ ያደርጋል
- ✓ በዞኑ ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች የተሰጠውን ግብዓት በአይነት፤በመጠን እና በብር ለይቶ ይይዛል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል፤
- ✓ የከረመ ግብዓትን በተመለከተ ከ ዞኑ ግብርና መምሪያ ጋር በጋራ መረጃ ያጠናቅራል
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ የዩኒየኖችን ማርጅን በዞኑ ግብአት አስተባባሪ አማካይነት እንዲወሰን ድጋፍ ይሰጣል
- ✓ በዞን ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

**የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ዞን ጽ/ቤት፤**

- ✓ ለግብርና ግብዓት ሽያጩ በ ወረዳ የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ደረጃ የሚመደቡ ሠራተኞችን ቅጥር ይፈጽማል፣ ምደባ ያደርጋል
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ካዝና፣ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች፣ ኩፖን፣ የኩፖን መረከቢያ፣ የገንዘብ መቀበያና መክፈያ ደረሰኞች፣ ቅጻቅጾች ያሰራጫል፣
- ✓ በዞን ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

**ሁለገብ የህብረት ሥራ ማኅበራት ዩኒየን**

- ✓ የክልሉ ግብርና ቢሮ በሚያሳውቀው የግብርና ግብዓት ድልድል መሰረት ከግብርና ግብዓት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት (AISE) ጋር ውል በመያዝ ግብዓቱን ይረከባል፡፡
- ✓ የተረከበውን ግብዓት ከአሸናፊ የትራንስፖርት ድርጅቶች ጋር ውል በመያዝ ከማዕከላዊ መጋዘን በድልድሉ መሠረት ወደ የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ያጓጉዛል፡፡
- ✓ ለመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ባቀረበው ግብዓት ልክ ውል ይፈጽማል
- ✓ ከእያንዳንዱ መሠረታዊ ማህበር በሚቀርብለት ዝርዝር የግብአት ሽያጭ የሂሳብ ሪፖርት መሰረት ከገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት ጋር ሂሳቡን ያመሳክራል የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት አዳም ያቀናንሳል
- ✓ የዩኒየኑን ማርጅን ከገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይረከባል
- ✓ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ሲታዘዝ በዱቤ ሽያጭና ግዥ የግብአት ዝውውር በዚህ መመሪያ በተገለጸው አሰራር መሰረት ይፈጽማል
- ✓ የዞን ቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

### *7.3 በወረዳ ደረጃ*

**አስተዳደር**

- ✓ አርሶአደሩን ስለግብአት አጠቃቀም መከስቀቀና ማስተማር እንዲሁም በአርሶአደር ምልመላ ወቅት የነቃ ተሳትፎ ማድረግ
- ✓ የቀረበው ግብአት ለታለመለት አላማ መዋሉን መከታተልና ድጋፍ ማድረግ
- ✓ አርሶአደሩ የወሰደውን ብድር በወቅቱ እንዲመልስ ዕገዛ ያደርጋል
- ✓ ወደ ኅ/ሥ/ማኅበራት ለሚጓጓዘው ግብአት የመንገድ ሁኔታና የትራንስፖርት ፋሲሊቲ ማመቻቸት

- ✓ ኅ/ሥ/ማኅበራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማጠናከር ፣ ማኅበራት በሌለባቸው አከባቢዎች እንዲቋቋሙ አቅጣጫ መስጠትና ክትትል ማድረግ
- ✓ በግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት የአራትዮሽ ውል ይይዛል
- ✓ ሕገ ወጥ የግብዓት ንግድ ዝውውሩን ይቆጣጠራል፤
- ✓ ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የሚላከውን የግብዓት እና ብድር ዕቅድ በግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴ አስገምግሞ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል
- ✓ ለህ/ስራ ማህበራትና ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ለመስረተ ልማት ግንባታ አገልግሎት የሚሆን ቦታ ያመቻቻል።
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

**የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት**

- ✓ በተለያዩ አበዳሪ አካላት በወረዳው ውስጥ የተሰጠውንና የተመለሰውን እንዲሁም ቀሪ ብድር የጠራ መረጃ ይይዛል፤
- ✓ የወረዳው ግብአት ዕቅድ በአርሶአደሩ ፍላጎትና የመፈጸም አቅም እንዲሁም ምርታማ በሆኑና በገበያ ላይ አዋጭነት ባላቸው የምርት ተግባራት ላይ ተመስርቶ እንዲታቀድና ተግባራዊ እንዲሆን ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤
- ✓ ግብአቶች ወደ ማኅበራቱ እንዲጓጓዙና ርክክቡ እንዲፈፀም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
- ✓ የግብዓትእጥረትና ክምችት ያለባቸውን አካባቢዎች በመለየት ለግብዓት ዝውውር መነሻ ሃሣብ ለወረዳው የግብዓትና ብድር አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለዞን ግብርና መምሪያ በወቅቱ ያሳውቃል፤
- ✓ በወረዳው በየዓመቱ ከሚቀርበው ግብዓት ጋር የተገናዘበ የመጋዘን ግንባታ በተለይም በህብረት ሥራ ማህበራት በኩል እንዲሰራ ያስተባብራል፤
- ✓ ከልማት ጣቢያ /ቀበሌ/ የቀረበለትን የግብዓት ዕቅድ የመፈጸም አቅምን በማገናዘብ ገምግሞ ለወረዳ አስተዳደር፤ለወረዳው የግብዓትና ብድር አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለዞን ግብርና መምሪያ በወቅቱ ያቀርባል፤
- ✓ ስለ ግብዓትና ብድር አሰጣጥ፣ አጠቃቀምና አመላለስ የሚወጡ መመሪያዎች በአርሶ አደሩ ግንዛቤ እንዲያዝባቸው ለማድረግ ያስተምራል፤
- ✓ በምርት ዘመኑ ሳይሰራጭ የከረመ ግብዓትና ቴክኖሎጂ በጥንቃቄ መያዙን ይከታተላል። ለቀጣይ አመት ጥቅም ላይ የማይውሉትን እያጠና የውሳኔ ሃሳብ ለወረዳው አስተባባሪ ኮሚቴ አቅርቦ ያስወስናል፤
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ በወረዳ ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

**የወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት**

- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ በወረዳ ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

**የወረዳ ህ/ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት**

- ✓ በወረዳው የሚቀርቡ የግብዓት በቅርበት ሆኖ ከግብርና ጋር በመሆን ይከታተል ፤
- ✓ ለማህበራቱ የቀረበ ግብዓት ክትትል ያደርጋል፤ የከረመ ግብዓት መረጃ በተመለከተ ከወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ጋር በጋራ ይሰራል ፤
- ✓ መሰረታዊ ማህበራቱ ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጉ ድጋፍ ያደርጋል
- ✓ በወረዳው የተሰጠውን ግብዓት በአይነት፤በመጠን እና በአበዳሪ አካላት በመለየት ከስርጭት ጀምሮ መረጃ በማጥራት ከወረዳው ግብርና ጋር ይይዛል ፤ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል፤
- ✓ ዘላቂነት ያለው የግብዓት አቅርቦት ስርጭትና አጠቃቀም እንዲኖር በወረዳው ስር ያሉትን መሰረታዊ ማህበራት ያጠናክራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
- ✓ ከወረዳው ካሉ ሌሎች ባለድረሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤፤
- ✓ በምርት ዘመኑ ሳይሰራጭ የከረመ ግብዓትና ቴክኖሎጂ በጥንቃቄ መያዙን ከግብርና ጋር በመሆን ይከታተላል።
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ✓ በወረዳ ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

**የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ዩኒየን ጽ/ቤት**

- ✓ ለግብርና ግብዓት ሽያጩ በሳተላይት ጽ/ቤት ደረጃ የሚመደቡ ሠራተኞችን ከመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት አመራሮችና ቅጥር ሠራተኞች ጋር ያስተዋውቃል፣
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆን ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- ✓ የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ ለባንክ ተመላሽ ያደርጋል፡፡ ያስገባበትን የባንክ ደረሰኝ ቅጅ አገናዝቦ ለየኒየኖች ይሰጣል፡፡
- ✓ መንግስት ከበጀቱ ለባንክ የተካው እና የተዘጋ የግብዓት ገንዘብ ከዋና መ/ቤት በሚላከው ደብዳቤ መነሻነት ለወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ገቢ ያደርጋል
- ✓ ለዩኒየኖች የሚሰጠው የባንክ ደረሰኝ ከእያንዳንዱን መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር ገቢ የሆነውን የገንዘብ መጠን ስለማያመላክት እና ጥቅል ስለሆነ እያንዳንዷ የባንክ ደረሰኝ የያዘችው የገንዘብ መጠን ከየትኛው ህብረት ስራ ማህበር የተሰበሰበ መሆኑን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ አያይዞ ለዩኒየኑ ይሰጣል፡፡

- ✓ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የኩፖን ርክክብ ያደርጋል፡፡
- ✓ የዩኒየኖችና የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትን ማርጅን ክፍያ ይፈጽማል፡፡
- ✓ ለተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ካዝና፣ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች፣ ኩፖን፣ የኩፖን መረከቢያ፣ የገንዘብ መቀበያና መክፈያ ደረሰኞች፣ ቅጻቅጾች ያሰራጫል፣
- ✓ በወረዳ ደረጃ የሚቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሰራል

## *7.4 ቀበሌ ደረጃ*

**ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት**

- ✓ አርሶ አደሩን ስለ ግብዓት አጠቃቀም መቀስቀስ ማስተማር ፤ በአርሶ አደር ምልመላ ወቅት የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ፤
- ✓ የሚመለመሉ አርሶ አደሮችን የቀበሌ ነዋሪነትና ብድር የሌለባቸውና ብድር እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው መሆኑን፤ የመመለስ አቅምና ታማኝነት ያረጋግጣሉ ፤
- ✓ የቀረበው ግብአት ለታለመለት አላማ መዋሉን መከታተልና ድጋፍ ማድረግ ፤ ይደግፋል፤ለአርሶ አደሩ የተሰጠው ብድር በወቅቱ እንዲመ ለስ ይደግፋል
- ✓ ወደ ኅ/ሥ/ማኅበራት ለሚጓጓዘው ግብአት የመንገድ ሁኔታና የትራንስፖርት ፋሲሊቲ ያመቻቻል ፤
- ✓ ሕገ ወጥ የግብዓት ንግድ ዝውውሩን ይቆጣጠራል፤
- ✓ ከቀበሌ ግብርና ል/ጽ/ቤት የተላከውን የግብዓት ዕቅድ ገምግሞ ለወረዳ ያሳውቃል
- ✓ ለህ/ስራ ማህበራት ለመሠረተ ልማት ግንባታ አገልግሎት የሚሆን ቦታ ያመቻቻል፣ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣል።
- ✓ የግብርና ግብዓት ሽያጩና ብድር አመላለሱ የተሳለጠ እንዲሆንና የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

**የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት**

- ✓ እጅ በእጅም ሆነ በብድር ግብዓት ለሚገዙ አርሶአደሮች ከመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት በሚቀርብለት ወቅታዊ የግብዓት ዋጋ መሰረት ገንዘቡን ተቀብሎ የዕጅ በዕጅም ሆነ የብድር ኩፖን ይሰጣል፡፡ የሚዘጋጀው ኩፖን የአርሶአደሩን ስም፣ የግብዓቱን ዓይነት፣ መጠንና፣ ዋጋው የያዘ መሆን አለበት፡፡
- ✓ በብድር ግብዓቱን የሚገዙ አርሶአደሮችን ለዚሁ ተብሎ በገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት በኩል በተዘጋጀው ማስፈጸሚያ መመሪያ መሰረት ይፈጽማል
- ✓ ከመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትና ከቀበሌው አስተዳደር ጋር በቅንጅት ይሰራል

**. *መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትና ቅርንጫፎቻቸው***

- ✓ የከረመ ግብዓት ካለ መረጃውን በዓይነት፣ በመጠንና በገንዘብ መጠን በየምርት ዘመኑ በመለየት ለወረዳ ግብርናና ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጽ/ቤት በህጋዊ ደብዳቤ ያሳውቃሉ ፡

- ✓ በሚሰጠው ድልድል መሰረት ከዩኒየኑ ጋር ውል በመያዝ ግብዓቱን ይረከባል
- ✓ ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት ወቅታዊ የግብአት ዋጋ መረጃ ይሰጣል
- ✓ ከገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት አርሶ አደሩ በስሙ የተዘጋጀለትን ኩፖን ይዞ ሲቀርብ በኩፖኑ ላይ የተገለጸውን ግብአት በአይነት ፣ በመጠን እና የዋጋውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ተቀብሎ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት በንብረት ገቢና ወጭ አፈጻጸም መመሪያው መሰረት በሽያጭ ሰራተኛው አማካኝነት ግብአቱን ለአርሶ አደሩ ያስረክባል ፡፡
- ✓ ከእያንዳንዱ አርሶ አደር የተረከበውን ኩፖን በህጋዊ ደብዳቤ በማኅበሩ ገንዘብ ያዥ አማካኝነት ለገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት ቢያንስ በ 15 ቀን አንድ ጊዜ ያስረክባል ህጋዊ ደረሰኝም ይቀበላል ፤
- ✓ ከገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት የተረከበውን ደረሠኝ ኮፒ በማድረግና በማገናዘብ ከዝርዝር የግብአት ሽያጭ የሂሳብ ሪፖርት ጋር በሸኚ ደብዳቤ ለዩኒየኑ ፤ ለወረዳ ግብርና ጽ/ቤት እና ለወረዳው ኅብረት ስራ ማኅበራት ማስፋፊያ ተ/ጽ/ቤት ያስረክባል፣ ሂሳቡንም ያቀናንሳል
- ✓ ከቀበሌ አስተዳደር፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ የማህበራት አደራጆችና የገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤትና ከወረዳ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፡፡
- ✓ ከገጠር ቁጠባና ብድር ማህበራት ጽ/ቤት የድርሻውን ማርጅን ይረከባል

## ክፍል አራት

### 8. *መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ*

*ይህ መመሪያ ተግባራ የሚሆነው በክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊ ተፈርሞ ከጸደቀበትና ወጭ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ሆናል ፡፡፡፡*